# "መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ!" በታሪክ አጻጻፍ ስልትና የተዛቡ የሁነቶች ትንታኔ ላይ የተሰጠ ሙያዊ ሂስ*

**በሳሙኤል ኪዳነ፤አክሱም ዩኒቨርሲቲ**
bazen.axum@gmail.com

## እውን ግን ታሪክ ይከሽፋል?

የዚህ ጽሑፍ ዋና መነሻ የቀድሞው ቀዳማዊ ሃይለስላሴ ቆይቶ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመባል የሚታወቀውን ተቋም በጂኦግራፊ የትምህርት አይነት በአስተማሪነት ሞያ ለረጅም አመታት ያገለገሉ በአሁኑ ወቅት በጥሮታ የሚገኙትን በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ታህሳስ 2005 ዓ.ም "መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ" በሚል ርእስ ለህትመት የበቃውን መፅሃፍ ላይ የተነሱ ታሪካዊ ጉዳዮች ላይ ያለኝን የግል አስተያየት መሠረት በማድረግ መስተካከል ያለባቸውን ጉዳዮች ላይ መረጃን ብቻ መሰረት ያደረገ የሙያ ሂስ ለመስጠት ነው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ማን ናቸው? ለሚለው ጉዳይ ብዙ ማብራርያ ለመስጠት ባልደፍርም ሆኖም ግን እሳቸው በሙያቸው ያበረከትዋቸው ስራዎች ግን ምንድ ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ለዚህ ፅሁፍ አንባብያን ይረዳ ዘንድ በ2003 ዓ.ም ራሳቸው ካሳተሙት "አገቱኒ ተምረን ወጣን" በሚለው መጽሃፋቸው ተዘርዝረው የሚገኙትን ነጥቦች ማየቱ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለኝ።

እንግዲህ ልብ በሉ አሁን እያወራን ያለነው ስለ ታሪክ እና የታሪክ ኣፃፃፍ ስልቶችን ነው። በዚህም መሰረት በፕሮፌሰር መስፍን የተቀመጡትን ታሪካዊ ሁነቶች በታሪክ ኣፃፃፍ ስልት መነፅሮች ሲታዩ ምን ያህል እውነት ናቸው? ምን ያህልስ ተኮላሽተዋል? የሚለውን ፍርድ የአንባቢውን ብቻ መሆን ስላለበት ነው።

በታሪክ አጻጻፍና አተረጓገም ላይ መሰረት ያደረጉ በርከት ያሉ ፅሑፎች በመፃፍ የሚታወቁ በሙያው አንቱታን ያተረፉ የታሪክ ምሁራን እንደሚሉት የታሪክ ትምህርት ጣዕም በአንድ ተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ላይ የታሪኩን ምንጭ (source) ለመቶርገምና ሙያዊ ትንታኔ ለመስጠት ትኩረት ባደረጉ ግብረገብነት የተሞላቸው ክርክሮችና ሂሶች በሚከፍትዋቸው ኣዳዲስ የአስተሳሰብ ሃዲዶች ሰዎች ለበለጠ እውቀትን ፍለጋ የሚገፋፉ ሁኔታዎች የሚፈጥሩ በመሆናቸው ነው በማለት ያሰረዳሉ።[1]

---

* ይህ ጽሑፍ ለ 117ኛው የዓድዋ የድል በዓል የካቲት 22 2005 ዓ.ም በአድዋ ከተማ በ ዘ አዘር ፌስስ ኦፍ ኢትዮጵያ አስተባባሪነት ለተዘጋጀው መድረክ የቀረበ ጽሑፍ ነው።

እንደ አብዛኞዎቹ የታሪክ ትምህርት ምሁራን ጸሓፊዎች እምነት ከሆነ ታሪክ እንደ ልብወለድ ፅሑፍ አልያም እንደ ሌላ የፈጠራ ፅሁፍ መቸት  እያጣጣምክ የመሰለህን እያስገባህ የማይጥምኽን ነገርግን እውነተኛ ክዋኔ እየቆረጥክ የምትፅፈው ፅሁፍ አይደለም። በዚህ ረገድ ታዋቂው ኢትዮጵያዊ ሊቅ ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ አጼ ምኒልክና ኢትዮጵያ በሚለው መፅሐፋቸው እንዲህ በማለት ያስረዳሉ።

> *"የታሪክ፡ ትምሕርት፡ ግን፡ የሚጠቅም፡ የውነተኛ፡ ታሪክ፡ ትምህርት፡ ሲሆን፡ ነው። እውነተኛንም፡ ታሪክ፡ ለመጻፍ፡ ቀላል፡ ነገር፡ አይደለም፡ የሚከተሉትን፡ ሶስት፡ የእግዚአብሄር፡ ስጦታዎች፡ ያስፈልጋልና። መጀመርያ፡ ተመልካች፡ ልቦና፡ የተደረገውን፡ ለማስተዋል፡ ሁለተኛ፡ የማያዳላ፡ አእምሮ፡ በተደረገው፡ ለመፍረድ፡ ሶስተኛ፡ የጠራ፡ የቋንቋ፡ አገባብ፡ የተመለከቱትንና፡ የፈረዱትን፡ ለማሳወቅ። ያገራችን፡ የታሪክ፡ ጸፎች(ፀሃፊዎች)፡ ግን፡ በነዚህ፡ ነገሮች፡ ላይ፡ ሃጢአት፡ ይሰራሉ። በትልቁ፡ ነገር፡ ፈንታ፡ ትኒሹን፡ ይመለከታሉ፡ ለእውነት፡ መፍረድንም፡ ትተው፡ በአድልዎ፡ ልባቸውን፡ ያጠባሉ፡ ኣጻጻፋቸውም፡ ድብልቅልቅ፡ እየሆነ፡ ላንባቢው፡ አይገባም።"[2]*

ታሪክ በግብዝነትና በማን አለብኝነት የሚፃፍ ጉዳይ ሳይሆን እጅግ በረቀቀ አኳሃን እውነተኛ ጭብጥ የያዘ ጭብጡ ከተፃፈበት ሁነት በመንፈስ ያልተለየ መሆን አለበት።

ይህ ካልን እንግድያ አንድ ሁነት በታሪክ መዝገብ ሊፃፍ የሚችልበት የተለያዩ መንገዶች አሉ። በዚህም መሰረት አንድ ሁነት ሲፃፍ  በተለያዩ ወቅቶች ማለትም ድርጊቲ በተፈፀመበት ቀን፣ ሰዓት፣  አመት ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ ከአጭር ወይም ከረጅም አመታት በኋላ ሊፃፍ ይችላል። ነገር ግን ይህ ሊሆን የሚችለው ምንጭ እስካለው ድረስ ብቻ ነው።

በአንፃሩ ግን የአንዷት አገር ወይም ህዝቦች ታሪክ በግብዝነትና በማንአለብኝነት የተፃፈ እንደሆነ በይዘት ደረጃ ሊያካትታቸው የሚገባቸውን ነጥቦች በማጣመም ወይም በማንሸራፈፍ በትውልድ ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽእኖ አሻራ እጅግ የከፋ ሊሆን እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።[3] በዚህ ጉዳይ ላይ አለቃ ታዮ ገብረማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ የሚለውን መጽሐፋቸው የጻፉበትን ዋና ምክንያት ወይም ዓላማ እንዲህ በማለት ያብራራሉ "ይህንንም ታሪክ ስናወጣው ከልብ አንቅተን ከሕሊና አውጥተን ልብ ወለድ የፃፍነው አይደለም።"[4]

ከዚህ አንፃር ሲታይ የመጀመሪያዎቹ በአማርኛና ሌሎች ቋንቋዎች የተፃፉትን ታሪክ ቀመስ ፅሑፎች ላይ የሚታዩ በርከት ያሉ ችግሮች ሲኖሩዋቸው ከችግሮቹ ውስጥ ለአንድ ሃይማኖት

---

[1] John Tosh. The Pursuit of History 5th Edition (2010) , E.H. Carr. What is History (2008)
2 ገብረሂወት ባይከዳኝ አጼ ምኒልክና ኢትዮጵያ ገፅ.3.
[3] በዚህ ጉዳይ ላይ Gustavson Carl. G. *A Preface to History*. (USA: McGraw-Hill Book Company, 1955) the Novice Historian pp.1-11 እንዲሁም The Use and Misuse of History, pp. 164-178. በሚሉ ምዕራፎች ከላይ የተገለፀውን ሃሳብ በደምብ ያብራራሉ።
[4] አለቃ ታየ ገብረማርያም ገጽ 7 እይ

ብቻ ማዳላት፣ አንድ ብሄርን ብቻ ተኮር ያደረገ ታሪካዊ ይዘት ያለውን ፅሁፍ መሆን፣ የራስን ሃይማኖት ወይንም ብሄር እንደ ዋነኛ ተዋናይ በመቁጠር የሌሎች ህዝቦች ታሪክ ህዝቦቹ ራሳቸው ከሚያስቡበት አቅጣጫ በተቃራኒው መዘገብ ከብዙዎቹ በኢትዮጵያ የታሪክ አጻጻፍ ላይ የሚታዩ ችግሮች ጥቂቶቹ ናቸው። በዚህ ረገድ ከቀደምት ፀሓፊዎች ግንባር ቀደም ተወቃሽም ተወዳሽም ሲኖሩ[5] በእኔ እምነት አሁን የዚህ ጽሑፍ መነሻ ምክንያት የሆኑትን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በዚሁ ረድፍ ያሉ የህዝብ ታሪክ አፃፃፍ ስልት አራማጅ ተብለው ሊገለፁ ይችላሉ።[6]

ልብ ብሎ አጠቃላይ በእሳቸው የተጻፉትን "የታሪክ" መጻህፍት ለሚያነብ አንባቢ ከዛሬ 100 ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ታሪክ ጸሓፊዎች የነበረውን በሽታ እሳቸው ላይ ያየዋል። ምን አይነት የታሪክ ድግግሞሽ ኣልያም መገጣጠም እንደሆነ ባላውቅም እኔም ብሆን ገብረሂወት ባይከዳኝ የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሓፊዎች ባየበት መነፅር ፕሮፌሰር መስፍንን ሳያቸው ገብረሂወት ባይከዳኝ ከ100 ዓመት በፊት ከጻፈውና ከስር እንደሚከተለው እንደተገለጸው ልዩነት ኣላገኘሁባቸውም።

> *"የታሪካችንም ጻፎች ሁለት ዓይነት ሰዎቾ እንደሆኑ እንረዳለን። አንዱ ዓይነት የቤተመንግስት ሊቃውንት ይባላሉ ማለት እንጀራን ሲፈልጉ ከቤተ መንግስት ተጠግተው ንጉሱ ያዘዛቸውን የራሱን ውዳሴ ታሪክ ብለው ፅፈው ለኋላው ትውልድ የሚያስቆዩ አቆላማጮች። ሁለተኛው ዓይነት ግን መነኮሳት ናቸው። እነሱም የሚጽፉት ታሪክ አድልዎ ይበዛበታል የራሳቸውን እንጂ የሕዝቡን ጥቅምና ጉዳት ከቶ አያቃጥሩምና ስለዚህ የልባቸውን የሚፈፅምላቸው ንጉስ ቅዱስ ቅዱስ ይሉታል ከዱንቁርናቸው ወጥቶ ከፍ ባለ ሕሊና ተመርቶ ስለዜጎች ልማት የሚጥር ግን ርኩስ።"[7]*

---

[5] በታሪክ አጻጻፋቸው በሚታዩ ክፍተቶች ከሚወቀሱ ቀደምት ጸሓፊያን ውስጥ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረየሱስ(የመጽሐፍ ርዕስ ጦቢያ) እኚህ ሰው በኢትዮጵያ የታሪክ ምሁራንና ተማሪዎቾ የሚታወቁባቸው ሁለት ነጥቦች ሲኖሩ እነሱም ለስልጣን ከነበራቸው ጉጉት የተነሳ ከኢጣልያ መንግስት ወራሪ ሰራዊት ጋር የነበራቸው ጥምረትና በኋላም የቄሳር ንጉስ መልእክተኛ ተብለው ሲሰሩት የነበረውን ወገንን የማስጠቃት ስራና ሁለተኛው ጉዳይም በሌሎች ብሄሮች በተለይም በብሄረ ትግራይ ላይ ሲያራምዱት የነበረውን ጨለምተኛ አመለካከት ጎልቶው ይታወቃሉ፣ አለቃ ታየ ገብረማርያም(የመጽሐፍ ርዕስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ) በተለይም የአማራን ነገድና የሌላውን የኢትዮጵያ ህዝቦች ነገዶች የገለፁበት መንገድ ምን ያህል የተዛባ አመለካከት እንደነበራቸው ጎልቶ ይታያል፣ አጽሜ ጊዮርጊስ እኚህ ጸሓፊ የኦሮሞ ብሄረሰብ ላይ የሚሰጡትን ትንታኔ ትዝብ ውስጥ ያስገባቸው ጉዳይ ነው።

[6] የህዝብ ታሪክ ኣፃፃፍ ስልት ከአካዳሚያዊው የታሪክ አፃፃፍ ስልት የሚለይበት ዋነኛ ምክንያት ዜጎች ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላኛው ትውልድ እውነት ነው ብለው የሚያምኑበትን ሃሳብ በቅርፅም በይዘትም ለውጥ ሳይደረግበት ለአንባቢያን የሚቀርብበት የአፃፃፍ ስልት ሲሆን የአካዳሚያዊው የታሪክ ኣፃፃፍ ስልት ግን ምንጭን መሰረት ያደረገ ትንታኔ የሚሰጥበት አሰራር ስለ ሆነ በቅርፅም በይዘትም የተለየ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ በፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ኢትዮጵያዊነት ልማት በኅብረትና፤ ኢትዮጵያ ከየት ወዴት? በሚል ርዕስ የተጻፉትን ጽሑፎች በመመልከት ብቻ የታሪክ ሙሁራን ሃሳባቸውን መስጠት ይችላሉ። በሌላ መልኩ መያዝ ያለበት ነጥብ ግን በሕዝብ ታሪክ አጻጻፍ ላይ ጸሓፊዎችን የሚወቅስ አካል እንዳለ ሁሉ እነሱንም የሚያወድስ አካል መኖሩን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነጥብ ነው።

[7] ገብረሂወት ባይከዳኝ ገፅ 3 እይ

በነጋድራስ ገብረሂወት ባይከዳኝ ዘንድ ቀደም ሲል ተጽፎ እንደምናገኘው "ዝቅ ብሎ ጠፍቶ የነበረው መንግስታችን ባባ ታጠቅ ቴዎድሮስ ሲታደስ በወሬሳው ካሳም ሲወሃድ እንዴት እንደነበረ ባባ ዳኘው ምኒልክም እንዴት አርጎ ሰፍቶ እንደረጋ ገልጾ የሚያወጋን የታሪክ ጸሐፊ ከቶ መቼ ይወጣ ይሆን"[8] እንደተባለው ሁሉ በጣም የሚገርመውና ለአንባቢም ለመቀበል የሚከብደው ነጥብ ግን አጼ ዮሐንስ የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ የሰሩትን ስራ በሙሉ ብቻቸውን አይወጡትም ነበር ተብሎ በተጠቀሰው ነጥብ ላይ አጠቃላይ ለኢትዮጵያ አንድነት የተደረገውን ትግል ንጉሠ ነገሥቱ ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ በንጉሠ ነገሥቱ ስር ሲተዳደሩ የነበሩትን አካላት ከፍ ለማድረግ የተጠቀሙበት አካሄድ ትዝብት ውስጥ ሳይከታቸው እንደማይቀር ለመግለጽ እወዳለሁኝ።[9]

እንደ አበዛኛዎቹ የታሪክ ጸሓፊዎች እምነት በርከት ያሉ ታሪካዊ ክስተቶች ለመለየት እጅግ በሚያስቸግር መልኩ ተመሳሳይ ባህርያት ይዘው በተለያዩ ወቅቶችና ቦታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። ከዚህ በመነሳት በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ጥናት ለሚያካሂዱ ምሁራን ይህንኑ የአሁኑ የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ራሳቸውን ከቀደምት የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሓፊያን በተለይም ከጦቢያው ደራሲ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረየሱሰ ለይቶ ለማየት በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል። ለአብነት ያኽል ፕሮፌሰር አፈወርቅ በገብረሂወት ባይከዳኝ በሚከተለው መልኩ ይተቻታሉ

> *"ያ ካቶ ኣፈወርቅ እጅ የታተመ ታሪክም ቢሆን ምሉ አይደለም። ብዙውን ነገር በጨለማነት ይተዋል ብዙውንም ነገር ያሳምራል በየዋሁ በጠንካራውም የትግሬ ነገድ ይልቁንም በንደ ወሬሳ ካሳ ያለ አርበኛ ከማንም ሰው እንጅ እንደ አቶ አፈወርቅ በሊቅነት ከተጠራ ሰው እጅና አፍ ሊወጣ የማይገባው የስድብ ቃል ይገኝበታል። ዳግማዊ ምኒልክን ለማመስገን ዳግማዊ(አራተኛው ዮሐንስ ማለታቸውን ነው) ዮሐንስን መስደብ የሚያስፈልግ ይመስላል።"[10]*

በሌላው መልኩ በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ከተነሱ "አጨቃጫቂ" ነጥቦች አንዱ በትግራይ ነበር ስለሚባለው የሽፍተኝነት ጉዳይ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን ሽፍተኝነት የብሄረ

---

[8] ገብረሂወት ባይከዳኝ ገጽ 4 እይ
[9] መስፍን "መክሸፍ…" ገጽ 166 እይ
[10] ገብረሂወት ባይከዳኝ ገጽ 5 እይ

*ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የማእከላዊ መንግስት የትግራይ መኳንንት እየወሰደ በእስር ማስቀረት ሲጀምር በእንደርታ እንዲህ የሚል ግጥም ይገጠም እንደነበር ፊታውራሪ እያሱ አፅብሃ በሐምሌ 1993 ዓ.ም አውግተውኝ ነበር፤

ከመይ ኢኩም ዓዲ ደጃች ድምፁ፤
ደጊም የለን ጮማታት ቁረፁ፤
ደጊም የለን መዓራት በፅብፁ፤
መቃብርኩም ሽዋ ተሃኒፁ፤
ዝገብኡ እምበር አይረአናይ ልወፁ።

ትግራይ የተለየ “የስራ መደብ” አድርገው ማቅረባቸው* እስካሁን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በርእሱ ላይ ጠለቅ ያለ ምርምር ካደረጉት እንደ R.A. Caulk ያሉ ሙሁራን ከፈር የለቀቀ ትንታኔ ነው። እሳቸው ኣዳዲስ ሃሳብ ይዘው በመጡ ባልከፋ ነበር ዳሩ ግን ያልነበረንን ተቀጥያ ተሰጥቶት ከእውነት ሊያንሸራትተን የሚችል ሃሳብ መሆኑን ነው። እስከ አሁን በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አብዛኞዎቹ እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ ላይ ወደ ስልጣን የወጡ ነገስታት የኋላ ታሪካቸውን ያየን እንደሆነ ከሽፍተኝነት የተቆራኘ ሆኖ እናገኘዋለን። ለአብነት ያኽል አጼ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ተብለው እስከ ተሾሙበት ጊዜ እሳቸውን ጨምሮ በርካታ በሰሜን፣ በሸዋ፣ በቤጌምድር(ጎንደር)፣ በወሎና በትግራይ የሽፍተኝነት ኑሮ የቀመሱ ሽፍቶች በኋላ ነገስታት ሆኖው ብቅ ብለዋል። ለዚህ አባባላችን ማሰሪያ ይሆን ዘንድ R.A. Caulk ይህንን አስመልክቶ እንዲህ በማለት ጽፎ እናገኘዋለን፡

> *“Everywhere in the Christian empire in the nineteenth century, government troops, tax assessors, and all travelling on official business to and from the court or the residences of provincial governors lived off the country side. Booty supplied the bounty by which lords bound retainers. Outlawry was an avenue to office frequently pursued by neglected members of the office-holding families….. The most renowned shefta have been malcontents from the local office-holding families who made up the provincial gentry in the Christian highlands. Some of these families had such wide ranging connections by marriage as to form a provincial nobility.”*[11]

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሆኖ የአጼ ምኒልክ ጸሐፌ ትእዛዝ በመሆን የአጼ ምኒልክን ዜና መዋእል የጻፉትን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ አጼ ምንሊክ በድጎረ መተማ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ከመጠራታቸው በፊት በተለያየ መልኩ በአጼ ዮሐንስ 4ኛ ከሚመራው ማእከላዊ መንግስት ሲያምፁ ወይም ሲሸፍቱ እንደነበር የሚያመላክቱ ፕሮፌሰር መስፍን ሽፍተኝነት ብለው ከጠቀስዋቸው ስራዎች በመንፈስ በፍፁም የማይለዩ ተግባራት እናያለን። ለዚህ ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም መፅሃፍ ውስጥ ያልተካተተው የምኒልክ የሽፍተኝነት ኑሮ በጸሓፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ በእንዲህ መልኩ ተፅፎ እናገኘዋለን።

> *"አጼ ቴዎድሮስ በ፲፰፻፷ ዓ.ም ከሞቱ በኋላ ግን ንጉሥ ምኒልክ ሸዋንና ወሎን በግዛት ይዘው በንጉሠ ነገሥትነት ስም እየተጠሩ ለ፲ ዓመት ያህል ቆዩ የዚያን ጊዜ ማንተማቸውም "ሞዓ አንበሳ*

[11] R.A. Caulk. Bad Men of the Borders: Shum and Shifta in Northern Ethiopia in the Nineteenth Century, pp. 40-41.

*ዘእምነገደ ይሁዳ ምንይልክ ንጉሠ ነገሥት" የሚል ነበር።" እንዲሁም*

*"በ፲፰፻፸፬ ዓ.ም ግንቦት ፴ ቀን እምባቦ ላይ ከጎጃሙ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ተዋጉ በዚህም ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ድል አድርገው ማረኳቸው።"*[12]

በእነዚህ ሁለት ነጥቦች መሰመር ያለበት ዋና ጉዳይ ንጉሥ ምኒልክ አፄ ቴዎድሮስ ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ አፄ ተክለጊዮርጊስና አፄ ዮሐንስ 4ኛ ወደ ስልጣን እስከመጡት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ጊዚያቶች ንጉሡ ምኒልክ በሁለቱም ላይ ለተከታታይ አስር አመታት አልገባም ብለው ሲሸፍቱ እንደነበር የማይካድ እውነት እንደሆነ፤ በተጨማሪም የጎጃሙን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለአፄ ዮሐንስ ገብተው እያለ እሳቸውን በጦር መውጋቱ በአጃ ዙር አፄ ዮሐንስ 4ኛ ሲወጉ እንደነበር የሚያመላክቱ የሽፍተኝነት ተግባራት ናቸው።

እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው ግን የትግራይ ሕዝብ የሽፍተኝነት ኑሮ አንገሽግሾት አፄ ቴዎድሮስ በግዛታቸው ሲያደርጉት የነበረ አረሜናዊ ስራዎች የከፋ ቢሆንም አጼው የትግራይን ህዝብ ከውቤ እና ከአገው ንጉስ ስለታገዱዋቸው ለማእከላዊ መንግስት እጅግ የከበረ ምስጋና እንደነበራቸው ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ዓብየዝጊ ወይንም በብዕር ስማቸው አለቃ ዘወልድ ታሪክ ጦቢያ በሚል የመጀመርያው በትግርኛ የተጻፈ የታሪክ መጽሃፋቸው ላይ ሰፍሮ ይገኛል።[13]

በሌላ መልኩ ግን እንደ R.A. Caulk አገላለጽ አብዛኛዎቹ የሽፍተኝነት የታሪክ ሁነቶች በተለይም ከደጌኞቹ በግብርና የተሰማሩ የክርስትያን ነገሥታት ይዞታዎችና አጎራባቾቻቸው ከነበሩ ወደ ቀይ ባህር የተጠጉ የሙስሊም ይዞታዎች በሚገኙ ቦታዎች ውጭ የሽፍተኝነት ታሪክ በተገቢው መልክ ለታሪክ ጸሐፊዎች እንደ ግብአት ሊሆን በሚችል መልኩ ተጽፈው አናገኛቸውም።[14]

ሌላው በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም መጽሐፍ የተካተተው ርእሰ ጉዳይ በአፄ ቴዎድሮስ እና በካሳ መርጫ በኋላ አፄ ዮሐንስ መካከል የነበረውን ፀብ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን የነዚህ ሁለት ገዢዎች የተለያየ ባህሪ ለአንባቢ ሳያስነብቡ በቀጥታ ዘለው የሚገቡት የግጭቱን ምንጭ በመተው ወደ ግጭቱ ሂደትና ውጤት ነው። ይህ ለአንባብያን ወደ ፍፁም ጨለምተኝነት የሚያሸጋግር አካሄድ ትክክል እንዳልሆነ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በመሰረቱ የመይሳው ካሳ እና የካሳ መርጫ ግጭት መታየት ካለበት በወቅቱ የነበሩትን ሶስት ዓበይት ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በዚህም መሰረት በወቅቱ የነበረውን አለም አቀፍ ሁነት፣ የመይሳው ካሳ የባህሪ ለውጥና ያስከተለው የሕዝብ ቁጣ እንዲሁም በወቅቱ ካሳ መርጫ ልክ እንደ ወላጃቸው የሚያይዋቸውን የእንደርታው ገዢ ደጃች አርአያ ድምፁን በመይሳው ካሳ መቅደላ ላይ ተወስደው መታሰር የተፈጠረው ቁርሾና የመበቀል ስሜት ናቸው። በተለይም

---

[12] ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ገጽ
[13] ደብተራ ፍስሃ ጊዮርጊስ ዓብየዝጊ፣ ታሪኽ ኢትዮጵያ፣ 1993 ገጽ 71 እይ
[14] R.A. Caulk p.40. በተጨማሪም ሽፍተኝነት በአከለጉዛይ፣ ሰራየ፣ ሰገነይቲ የተለመደ እንደነበር ያስረዳል። ገፅ 47-49 እይ

ከሶስተኛው ነጥብ በኩል የነበረውን የትግራይ መኳንንት ስሜት በወቅቱ የዓለም የሽርክና ዲፕሎማሲ ትስስር መሰረት የነበረውን የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው የወዳጄ ጠላትም ጠላቴ ነው የሚለውን አስተሳሰብ በተገቢውን ቦታ ሊያስተናገድ የሚችልበትን ሁነት እንዲፈጠር አስችሎታል።[15]

ከላይ ከጠቀስነው ነጥብ በተቃራኒ አጼ ቴዎድሮስ ትግራይን እጅግ ይወድዋት እንደነበር በተለያየ መልኩ ይገለፃል። እንደ ታሪክ ጸሐፊዎች ዘገባ ከሆነ ግን የአጼ ምኒልክ ስሜት ከተመለከትን በተቃራኒው ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህ ጉዳይ ላይ ነጋድራስ ገብረሂወት ባይከዳኝ እንዲህ በማለት ጽፈው እናገኛቸዋለን፤

> *"ትግሬ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ፈጽሞ ጠፍተዋል። የትም የትም ብትሄድ በዛች አገር የለማ መንደር አታገኝም። ሰው ከሚኖርባቸው ጎጆዎች ይልቅ የድሮ ልማትዋን የሚመሰክሩ ፍራሾችዋ ይበዛሉ። የትግሬም ጎበዝ በዛሬ ዘመን ባባቱ አገር አይገኝም አውራ እንደሌለው ንብ ድርሻው ሳይታወቅ ወደ አራት የዓለም መዓዘኖች ተዘርተዋል እንጂ። ባገሩም ላይ ድህነት ሰፍታለች የሌሎች ወገኖች መተረብያ እስክትሆን ድረስ። ሁሉም መሬት በሰላም ሲኖር ምስኪኒቱ ትግሬ ግን ሽፍታና ወንበዴ አልተለያትም።"[16]*

በፕሮፌሰር መስፍን አጼ ምኒልክ ቂም የለሽ ደግ መሪ ነበሩ ተብሎ የተጻፈው[17] አጼ ምኒልክን ለመካብ እንዲሁም እሳቸው የተጋዙበትን የአስተሳሰብ ሃዲድ በእሳቸው ዘመን እንደ ቅፅበት የተፈጠረ ተደርጎ ለማሳየት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም። እውነታው ግን አጼ ምኒልክ እጅግ የከፉ ቂመኛና በቀለኛ እንደነበሩ የሚገልጹ ጽሑፋች አሉ። ለአብነት ያክል የሸዋ ሰው ከጎጃሞችም በተዋጉ ቀን እየገደሉ ሲሰልቡ እንደነበር፤[18] እንዲሁም በአድዋ ጦርነት ወቅት ለኢጣልያ ገብረው የጠላት ወታደር በመሆን የተዋጉትን ኤርትራውያን እጅና እግራቸው መቁረጣቸውን ከዚያም በላይ እጅግ የሚዘገንነው ግን የአጼ ምኒልክ ሰራዊት ወደ ትግራይ በዘመተበት ወቅት ትግራይ ላይ ያደረሰውን ውድመት በአብዛኛዎቹ የታሪክ ፀሃፊዎች ለምን ተቆርጦ እንደሚተው ባላውቅም በጻሐፊ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ የተጻፈውና ከዚህ በታች የተዘረዘረውን አንባቢ እንዲያውቀው ማድረጉ ህሊናን ይፈታተናል የሚል እምነት የለኝም።

> *"የሰራዊቱም ብዛት ልክ መጠን የለውም ነበርና ተከፍሎ እንዲጓዝ ንጉሱ ከዛው ውሎ አድርገው ራስ ሚካኤልንና ራስ ወሌን ቱርክ ባሻ ታምሬን ደጃች መኩርያዮን ፊታውራሪ ተክለ ማርያምን ደግሞ ሌሎች መኳንንት ተጨምረው ቀድመው ተጓዙ። አጼ ምኒልክ ግን*

---

[15] ፍስሃ ጊዮርጊስ ዓብየዝጊ፣ አጼ ቴዎድሮስ ትግራይ እጅግ ከልባቸው ከመውደዳቸው የተነሳ "ትግራይ ዓደይ ይብልዋ ነበሩ" ትግራይ ሃገሬ ገጽ 71 እይ

[16] ገብረሂወት ባይከዳኝ ገጽ 9 እይ

[17] መስፍን "መክሸፍ ...." ገጽ 166-167 እይ፤ ገብረ ስላሴ፣ አጼ ምኒልክ መጋቢት በ፺ ቀን ሐረማት መሬት አጐዲ ላይ ራስ መንገሻ ሲገቡላቸው ትግሮችና ኢጣሊያኖች ጠብ ናቸውና እንድይገናኙ ከመረብ ወዲህ ራሰ መንገሻን ሹመው ሸልመው ከመረብ ወዲያ ደጃች መሸሻን የሸሙበት ዝርዝርገጽ 171 እይ

[18] ገብረ ስላሴ ገጽ 106 እይ

*በየካቲት መባቻ በ፲፮ኛው ቀን መቀሌ ካጼ ዮሐንስ ከተማ ገቡ።.... ከዚህ በኋላ በየካቲት ፳፭ ቀን ተነስተው አብርሃ አጽብሐ ሰፈሩ በ፳፯ ውሎ ሆነ።" አገሩ ሁሉ ገብሮ የሚዘረፍ ታጥቶ ሠራዊቱ ተርቦ ነበር። በ፳፱ አጽቢ ዕዳ ስላሴ ሰፈሩ። የባላገሩ ብዙ እህል ተገኝቶ ነበርና ሰራዊት ስንቁን አነሣ።"*[19]

እዚህ ላይ አንባቢያን አጽንኦት መስጠት ያለባቸው ጉዳይ ሰራዊቱ መብዛቱ ብቻ ሳይሆን ያገኘውን ሁሉ እየቀማና እየዘረፈ መሄዱ ሳያንሰው ለዘመናት ሳይደፈሩ የኖሩትን ከተከታታይ የእሳት ቃጠሎ ፍርድ የተረፉትን አድባራትና ቤተክርስትያናት ተዘርፈዋል። ከነዚህ ውስጥ ግንባር ቀደም ተጎጂ የሆነው የአብርሃ ወአጽብሃ ቤተክርስትያን አንዱ ነው።

በፕሮፌሰር መስፍን ምኒልክን የስልጣኔ መሪና በመቻቻል የሚያምኑ ተደርጎ ለተቀናበረው ሃሳብ በተቃራኒው ያለው እውነት የሚያሳየን ግን አጼ ምኒልክ የመንግስታቸውን አጠቃላይ አሰራር ምን ያህል ከድሮው የአስተሳሰብ ድር ጋር ተሳስሮ እንደቀጠለ ገብርሂወት ባይከዳኝ እንዲህ በማለት ገልጸዋቸዋል፤

> *"አጤ ምኒልክ በእውነት የሸዋ ሰውና አቶ አፈወርቅ እንደሚሉት አዲስ ሕግጋት አውጥተዋልን፣ ትምህርትስ ገልጸዋልን፣ እውነት አይደለም ይህማ ቢሆን ይህን ያህል ጊዜ በሰላም እንጀራቸውን አይበሉም <u>ነበር።...የሸዋው ንጉስ ግን ለሕዝባቸው ያባቱን ልማድ መረቁለት አዲስ ነገር እንዲቀበላቸውም አልተከራከሩትም</u>።"*[20]

ከዚህ ነጥብ እንካን ብንነሳ አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያ በአጼ ቴዎድሮስ ፊታውራሪነት የጀመረችውን የለውጥ ጉዞ በተጀመረበት ፍጥነት እንዳይቀጥል ያቅማቸውን መስራታቸውን ያሳየናል። እንዲያውም ይባስ ብሎ ሕዝብና አገሪትዋን ለረጅም አመታት የሚቆይ ቁርሾ Land Concession ተብሎ ወደሚታወቀው የፖለቲካ ቁማር ነበር የገቡት። ይህም ጉዳይ የመክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ዋና አርእስት ሳይሆን መቅረቱ ሾላ በድፍኑ እንደሚባለው አይነት ያስመስለዋል።

ሌላው ጉዳይ ስለቂም ከተነሳ ፕሮፌሰር መስፍን እንዲህ በማለት አስነብበውናል

> *"በትረ መንግስት ከአፄ ዮሃንስ ወደ አፄ ምንሊክ ሲተላለፍ አንዳንድ ለውጦችን አስከትሎኣል፤ በመጀመርያ የአፄ ዮሃንስን ተከታዮችናዘመዶች ማስኮረፉ ከቴዎድሮስ ጀምሮ ብዙ መስዋእት የተደረገበትን አንድነት አደጋ ላይ ጥሎታል፤ በትግራይ መሳፍንትና*

---

[19] ገብረ ስላሴ ገጽ 169-170 እይ

[20] ገብረሂወት ባይከዳኝ ገጽ 10-12 እይ

> *መካንንት መሃከል በአንድ በኩል በአደረባቸው <u>የስልጣን ምኞት</u>፣ በሌላ በኩል <u>በኢጣልያኖች በሚደረገው በገንዘብና በመሳሪያ የመደለል ዘመቻ</u> ሰፊ ለዩነት ተፈጥሮ ነበር።"*[21]

በዚህ ረገድ በቁጥር በርከት ያሉ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ሚሚያ ጸሑፎች ተጽፈው እናገኛለን። ከሁሉም በላይ ግን የቀድሞው የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህር የነበረው አቶ መኮንን ብርሃነ የጻፈውን ጽሁፍ ውስጥ የተካተቱ አበይት ቁም ነገሮች ጋር የሚጋጭ ሆኖ እናገኘዋለን።[22] በመሰረቱ አጼ ምኒልክ በትግራይ ሲከተሉት የነበረውን ፖሊሲ በራሱ ሲተነተን ከፋፍለህ ግዛ ከሚለው የቄሰራውያን ኃይሎች ፖሊሲ ምንም አይነት መሰረታዊ ልዩነት የለውም። በዚህ ጉዳይ ላይ አንባብያን የበለጠ መረጃ ይኖራቸው ዘንድ የአጼ ምኒልክ መንግስትና የአጼ ሃይለስላሴ መንግስት በደጃች ጉግሳ አርአያስላሴና በራስ መንገሻ ዮውሐንስ እንዲሁም ቆይቶ በደጃዝማች ሃይለስላሴ ጉግሳና በራስ ስዩም መንገሻ ላይ ሲያራምዱት የነበሩትን የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲዎችን ማጤን ተገቢ ጉዳይ መሆኑን ለመጠቆም እወዳለሁኝ። ይህንን ካላደረግን ግን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ይሆንና ድሮ ሲነገረን እንደነበረው የሰምና ወርቅ ምሳሌ ግጥም[23] ትርጉሙ ሳይገባን መክረማችን ግድ ይለናል።

እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ የአጼ ምኒልክን ታሪክ ከመጀመሪያው ጀምረን በምናነብበት ወቅት ያሉትን አጠቃላይ ሁነቶች ከቂምና ከተንኮል የጸዱ ናቸው ብለን ብናስተምር የዋህነታችንን በአደባባይ እንደመግለጽ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ አይደለም። ይህንን ስህተት መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በሚለው መጽሐፍም በዚህ መልኩ ተደግሞ እናየዋለን።

> *"የአፄ ምንሊክ ዘመን የምንመለከተው ከአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመርያ አንስቶ በመላ ኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን ትልቅ ትርምስ በዚህም ሳቢያ ማእከላዊው መንግስት ተዳክሞ በዘመነ መሳፍንትና በአምባገነኖች ሃይል አገሪቱ ወደ <u>መከፋፈል</u> ደረጃ ተቃርባ እንደነበር በመገንዘብ ነው።"*[24]

በፕሮፌሰር መስፍን ዘንድ ከተጠቀሱት ነጥቦች አንዱ አጼ ዮሐንስ ከእንግሊዝ ሰራዊት ጋር የመሰረቱት ጥምረት አጼ ዮሐንስ ሲኖርበትም ሲገዙትም በነበረው አከባቢ ወገን ማስጠቃት

---

[21] መስፍን "መክሸፍ ..." ገጽ 141 እይ

[22] Mekonnen Berhane. *Political History of Tigray:* Shewan *Centralization Versus Tigrean Regionalism (1889-1910).* M.A. Thesis in History, A.A.U., 1994.

[23] ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ገጽ xiii እይ
ውላሞ ሲል አቤት አቤት
ሲዳሞ ሲል አቤት አቤት
ጋሞ ሲል አቤት አቤት
ትግሬ ኀረበጠኝ የጣልያን ኀረቤት።

[24] መስፍን "መክሸፍ ..." ገጽ 132 እይ

የተለመደ ተግባር ነበር ተብሎ የተጻፈው ነጥብ እጅግ መኮነን ያለበት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የዋሆች "እውነት ነው" በሚል የየዋህ አእምሮ ተሳስተው እንዳይደግሙት መረጃን አጣቅሶ መኮነን ያለበት ጉዳይ ነው። ያም ሆነ ይህ እውነቱ መነገር ካለበት በመክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ውስጥ  በዋቢ መጽሐፍት ስር ከተዘረዘሩት በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተጻፈውን በመካንንቱ መሃከል የነበረውን ግልፅና ተጨባጭ የመጠቃቃት ተግባራት እንደሚከተለው ተጽፎ እናገኘዋለን።

አፄ ምኒልክ በ1880 ታህሳስ 28 ደርቡሽን ለመውጋት አምባ ጫራ እንደዘመቱ በሚያትት የፅሑፋቸው ርዕስ ላይ ፀሓፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ እንዲህ ይላሉ

> "አጼ ምኒልክም መተማ አጠገብ ድረስ በያገሩ ቀለብተኛውን ምሪት አግብተው ከማህል ሰፋሪና ከዘበኛ ጋር በ፲፯ ቀን አምባጭራ ሰፍረው ፳፪ ቀን ተቀምጠው ከዚህ በኋላ ደርቡሽ ከምሽጉ የማይወጣ ቢሆን አጼ ዮሐንስም ከሰሐጢ ተመልሰው መቀሌ ከከተማዋ ገባሁ ብለው ቢልክብዎ ወደ ሸዋ ለመመለስ በግንቦት ፲፩ ቀን ተጉዘው ሚካኤል ደብር ሰፈሩ"[25]

በዚህ ነጥብ ላይ ፕሮፌሰር መስፍን ወገን ማስጠቃት ብለው ለገለፁት አባባል ምናልባትም አጼ ምኒልክ ከደርቡሽ ጋር ላለመዋጋት የወሰዱትን እርምጃ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል። በዚህም መሰረት ምኒልክ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች የደርቡሽን ሃይል ሳይዋጉት ተመልሰዋል እነሱም፤

1ኛ አጼ ዮሐንስ ወደ ሰሓጢ ያደረጉትን ዘመቻ በለስ ያልቀናቸው እንደሆነ ምንሊክ ከመተማ ወደ ትግራይ ለሚያደርጉት ጉዞ ሰራዊታቸውን እነደተጠበቀ እንዲቆይላቸው ከነበራቸው ፍላጎት

2ኛ አጼ ዮሐንስ ጣልያንን ሰሓጢ ላይ ድል አድርገው እንደሆነ በአንፃሩ ግን ንጉስ ምኒልክ በደርቡሾች ከተሸነፉ በሁለቱም በኩል የነበረውን ባላንጣነት በንጉስ ምኒልክ ሰራዊት መዳከም ምክንያት እንዲሁም አጼ ዮሐንስ ሰሓጢ ላይ ባገኙት የማሸነፍ ወኔ አጼ ምኒልክን ጠቅልለው ሊያሸንፍዋቸው የሚቹልበትን ዕድል ሊኖር ስለሚችል በሚሉ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

ከዚህ አንፃር የነበረውን ሁኔት በማይቀየር መልኩ ትክክለኛ ታሪካዊ ምልከታ ወይም ቅኝት ቢሰጠው ወገንን ለማስጠቃት በቅርብ ርቀት ላይ የነበረው ሰሓጢ ላይ ሲፋለም የነበረውን አጼ ዮሐንስና የትግራይ ሰራዊት ነው ወይስ መተማ ኣፋፍ ላይ ሰራዊቱን የሰልፍ ትርኢት ሲያደርግ የሰነበተው በንጉስ ምኒልክ የሚመራው የሸዋ ሰራዊት ነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት የትኛው ነው የሚያሻማው።

በአጠቃለይ ሲታይ የዚህ መጽሐፍ ይዘት በተወሰነ መልኩ ለመቃኘት እንድተሞከረው በይዘትም በታሪክ ሁነቶች አቀራረብም እጅግ ከፈር የወጣ ከመሆኑም በላይ ለአንድ ንጉሠ ነገሥት በማድላት እንዲሁም ኢትዮጵያዊነት በሕዝቦች ፈቃድ ሳይሆን በነገስታት ችሮታ ብቻ

[25] ገብረ ስላሴ ገጽ 150 እይ

የሚመነዘር ጉዳይ ተደርጎ ማቅረቡን፤ ከምንም በላይ ግን ጸሓፊው በአጼ የውሐንስና በብሄረ ትግራይ  ላይ ያላቸውን ጨለምተኛ አመለካከት በአደባባይ እንዲታይ ማስቻሉን አንባብያን የመሰላቸውን ፍርድ እንዲወስዱ ያስችላቸዋል። በመጨረሻም በጸሓፊው ስለ አጼ ዮሐንስ አሟሟት የተገለጸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ *ahistory* ተብሎ የሚገለጽ ጉዳይ ቢሆንም የጸሓፊው የሃልዮሽ ጉዞ ግን ወዴት እያመራ እንደሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም። *History shall remember kings but not soldiers* በሚለው አባባል ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በጻፉት ጽሑፍ ጽሑፌን አጠቃልላለሁኝ።

> *"ያገራችንም የታሪክ ጻፎች ውዳሴ ከንቱን ስድብ እውነተኛውን ታሪክ አይተው የማይመስለውን ተረት የሚወድ ባይሆን ምንም ባልጎዳነም ነበር። መጽሐፋቸውንም እንቦ እውነቱን መርምሮ ላማግኘት አእምሮ ላለው ሰው ባላስቸገረው ነበር። እጅግ ያሳዝናል እስካሁን ድረስ ያበሾች ታሪክ በጨለማ ተሸፍነዋልና።"*[26]

[26] ገብረሕይወት ባይከዳኝ ገጽ 4 እይ